
በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

ሕዝብና ቤት ቆጠራ




# የ1999 ዓ/ም የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ

አዲስ አበባ

ሚያዚያ 1999

## ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| I. መግቢያ | 1 |
| II. የትምህርትና ቅስቀሳ ዓላማዎች | 1 |
| III. ለትምህርትና ቅስቀሳ ተግባር እንዲውሉ የተዘጋጁ ዶክመንቶች | 2 |
| IV. የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት | 2 |
| 4.1 በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት | 3 |
| 4.2 በክልል ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት | 5 |
| 4.3 በዞን ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃፊነት | 6 |
| 4.4 በወረዳ ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት | 7 |
| 4.5 በቀበሌ ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት | 8 |
| V. ሁሉም ሊያውቀው የሚገባውን የህዝብና ቤት ቆጠራ መርሆዎች በተመለከተ | 9 |
| VI. የቆጠራ ቀን በዓል አከባበርን በተመለከተ ሊደረጉ የሚችሉ ተግባራት | 9 |
| VII. የመዝሙር አጠቃቀም | 10 |
| VIII. የፖስተሮች አጠቃቀም | 10 |
| IX. ብሮሹር አጠቃቀም | 11 |
| X. ተጨማሪ የቅስቀሳ ማዕከላት/ስልቶች | 11 |
| XI. ማጠቃለያ | 12 |

# የ1999 ዓ/ም የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ አፈፃፀም መመሪያ

## 1. መግቢያ

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባርን ለማስፈጸም የተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችን፣ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ወዘተ... ከፍተኛ ተሳትፎና ትብብር የሚጠይቅ ስለሆነ የሁሉንም አካላት በቂ ትብብር ለማግኘት ቅስቀሳ ማድረግ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይሆንም:: በተለይ የቆጠራው ውጤት ፍሬያማና ጥራቱ አስተማማኝ እንዲሆን መረጃውን የሚሰጠው ግለሰብ፣ ቤተሰብና በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ ስለ ቆጠራው ያላቸውን ግንዛቤ ማጉልበት ወሳኝነት አለው::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ግቡን ሊመታ የሚችለው የቆጠራው ሥራ ጠቀሜታ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ሲኖረውና እያንዳንዱ ግለሰብና ሕብረተሰብ ለሥራው በከፍተኛ ደረጃ ሲተባበር ነው:: በመሆኑም ቆጠራውን አስመልክቶ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሰፋት ያለው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ማካሄድ ያስፈልጋል:: ስለሆነም የቅስቀሳ ኮሚቴዎችን ከሀገር አቀፍ ጀምሮ፣ በክልል፣ እንዲሁም በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ በማቋቋምና በማደራጀት ወደ ሕብረተሰቡ መድረስ ያስፈልጋል::

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ የ1999 ዓ/ም ሦስተኛ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራን አስመልክቶ የተዘጋጁ ሰነዶችን በመጠቀም በተለያየ ደረጃ የሚካሄዱ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች ወደ ተግባር የሚለወጡበትን፤ ማን ምን መስራት እንደሚገባውና የቅስቀሳው ሥራ መቼና እንዴት እንደሚከናወን ግልጽና ወጥ አሠራርን ለማመልከት የተዘጋጀ ነው:: በዚህ መመሪያ ውስጥ የሠፈሩት ሀሳቦች ኤጀንሲው ባዘጋጃቸው የተለያዩ ዶክመንቶች ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ቢሆንም በዚህ መመሪያ ውስጥ በተቀናጀ ሁኔታ ቀርበዋል::

## 2. የትምህርትና የቅስቀሳ ዓላማዎች

የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ቀዳሚ ዓላማው ለቆጠራው አፈፃፀምና መሣካት የሕዝቡን ሙሉ ትብብር፣ ከፍተኛ ድጋፍና ተሳትፎ ለማግኘት ሲሆን ቆጠራው ከመካሄዱ በፊት ስለቆጠራው ምንነት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማሳወቅ ከታች በዝርዝር የተጠቀሱት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት::

- የሕዝብና ቤት ቆጠራ ምንነት በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ፣
- ከቆጠራው የሚገኙ መረጃዎችን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ለሕዝቡ በማስረዳት ከቆጠራው በፊት በሚደረጉ ዝግጅቶችና በቆጠራው ወቅት ግለሰቦችና ድርጅቶች ለሥራው መሳካት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- ሕዝቡ ትክክለኛውን መረጃ ለቆጣሪዎች በመስጠት ያልተቆጠበ ድጋፍና ትብብር ማድረግ እንዲችል ማስገንዘብ እና
- የቆጠራው ውጤት በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ማስተማርና ማሳወቅ የሚሉት ናቸው::

## 3. ለትምህርትና ቅስቀሳ ተግባር እንዲውሉ የተዘጋጁ ዶክመንቶች

ህብረተሠቡን ስለ ሦስተኛውና በ1999 ዓ/ም ስለሚካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ ለማሳወቅና ለመቀስቀስ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ ለዚሁ እንዲረዳ የተለያዩ የቅስቀሳ ማቴሪያሎች ተዘጋጅተዋል:: እነዚህም፣

1. የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ መሪ ሠነድ፣
2. ግጥሞች - በውድድር የተገኙ 3 ግጥሞች፣
3. ድራማዎች - በውድድር የተገኙና:-
   - በአማርኛ
   - በኦሮምኛ
   - በትግርኛ

   ቋንቋዎች - ለቴሌቪዥን እና
   - ለሬዲዮ በሚያመች መልኩ የተዘጋጁ ድራማዎች፣
4. ቡሮሹር - በጥያቄና መልስ መልክ የተዘጋጀ ቡሮሹር በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በትግርኛ ቋንቋዎች የተዘጋጁ፣
5. ፖስተሮች - በ5 ቋንቋዎች ማለት በአማርኛ፣በኦሮሚኛ፣በትግርኛ፣በአፋርኛና በሶማሊኛ የተዘጋጁ 5 ዓይነት ፖስተሮች፣
6. መፈክሮች - 10 የተለያዩ መፈክሮች ተመርጠው ተዘጋጅተዋል:: እነኚህ መፈክሮች በባነር ላይ፣ በስብሰባ አዳራሾችና በሌላ አስፈላጊ በሆነ ስፍራ ጥቅም ላይ ይውላሉ::
7. መዝሙሮች - በውድድር የተገኙ 3 መዝሙሮች
8. በየጊዜው በጋዜጦች ፊት ገጽ ላይ እንዲወጡ የተዘጋጁ የሚነበቡ ቆጠራውን የሚመለከቱ ልዩ ጽሑፎች/ መልዕክቶች
9. በየጊዜው በጋዜጦች የውስጥ ዓምድ ላይ እንዲወጡ የተዘጋጁ መጣጥፎች
10. ቆጠራውን የሚያንፀባርቅ መልዕክትና የተለያዩ ምስሎችን የያዘ የ1999 ዓ/ም ካሌንደር (የቀን ገበታ)
11. ቆጠራን የሚመለከቱ መፈክሮችን/መልዕክቶችን የያዘ የኪስ ማስታወሻ
12. የትምህርትና ቅስቀሳ አፈጻጸም መመሪያ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናሮች/ስብሰባዎች ላይ የቀረቡ ጽሁፎች ይገኛሉ::

## 4. የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት

የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚካሄድባቸውን ዘዴዎች የአፈፃፀም ሁኔታና በቅስቀሳ ሥራ ላይ የሚሳተፉ አካላትን በተመለከተ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ ላይ ከገጽ 28-33 በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን፣ ከሀገር አቀፍ በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም በቀጣይነት መከናወን ያለባቸው ዋና ዋና ሥራዎች ደግሞ ከዚህ በታች ተገልጸዋል::

## 4.1 በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

### 4.1.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ( ማ.ስ.ኤ )

ሀ. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመው ኮሚቴ ዋነኛ ተግባሩ ሕዝቡ ስለቆጠራው ያለውን ግንዛቤ ማሳደግና ስኬታማ ውጤት እንዲገኝ በክልል ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ማደራጀትና መቋቋሙን መከታተል፣

ለ. የክልል የቅስቀሳ ኮሚቴዎች ከኮሚሽኑ በተዘጋጀው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የቅስቀሳ ሥራዎችን ማከናወናቸውን መከታተል፣

ሐ. ለቅስቀሳው ተግባር የሚውሉ ፖስተሮችን፣ ቡሮሹሮችን፣ መዝሙሮችን፣ ድራማዎችንና መፈክሮችን ማዘጋጀት፣

መ. የተዘጋጁ ፖስተሮችን፣ ቡሮሹሮችን፣ መዝሙሮችን፣ ድራማዎችንና መፈክሮችን ለክልሎች ማሰራጨት፣

ሠ. በተለያዩ የክልል ስብሰባዎችና ሴሚናሮች ላይ በመገኘት ስለቆጠራው ግንዛቤ ሊያስጨብጡ የሚችሉ፤ ቃለ መጠይቆችንና የፓነል ውይይቶችን በተለያዩ የቅስቀሳ መድረኮችና የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ለአመራር አባላት እና ለሕብረተሰቡ የቆጠራውን የቅስቀሳ ሥራ ማከናወን፤

ረ. ለቅስቀሳው ተግባር የተዘጋጁ ድራማዎች፣ መዝሙሮችና ግጥሞች በተለያዩ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ለሕብረተሰቡ እንዲተላለፉ ማድረግ፤

ሰ. በብዙሃን መገናኛና በሌሎች የተለያዩ የብዙሃን መረጃ ማስተላለፊያና ቅስቀሳ ዘዴዎች በመጠቀም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽንን የሥራ ሂደትና እንቅስቃሴ፤ የተላለፉ ውሳኔዎችንና የሥራ አፈጻጸም መመሪያዎችን ለክልሎች ማሳወቅ፤

ሸ. የህብረተሰቡ ተሳትፎን ለማጐልበት በሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተጠቀሱ እንደ "መቆጠር መብትና ግዴታ" መሆኑን "ግዴታን አለመወጣት የሚያስከትለውን ቅጣት"ንና የመሳሰሉትን ድንጋጌዎች በተመለከተ ሕብረተሰቡ በተለያዩ የብዙሃን መገናኛና የቅስቀሳ ዘዴዎች እንዲያውቅ ማድረግ፤

ቀ. የ1999 ዓ.ም. ሶስተኛው የሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቆጠራ ቀን በዓል ግንቦት 20/1999 ዓ.ም እንዲከበር ማድረግ፤ አፈጻጸሙን መከታተል፤ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ሕብረተሰቡ የቆጠራው ቀጥታ ተሳታፊና ተባባሪ እንዲሆን በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ቅስቀሳ ማድረግ፣

በ. የቆጠራውን የመጀመሪያና የመጨረሻ ውጤት ለሕዝቡ በመግለጽ የመረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን በተለያዩ የብዙሃን መገናኛ፣ የቅስቀሳ መድረኮችና ዘዴዎች ተጠቅሞ መግለጽና የሪፖርት ዝግጅቱንና ስርጭቱን መከታተል ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

## የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና የቅስቀሳው ተግባራት መርሃ ግብር

| ሊካሄዱ የታቀዱ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች | ጊዜ |
|---|---|
| • ፖስተሮችና ቡሮሹሮችን ማሳተምና ማሰራጨት | ከመጋቢት 15/99–ሚያዚያ 30/99 |
| • የሬዲዮ ድራማዎች ዝግጅት | ከየካቲት 5/99 - መጋቢት 30/99 |
| • የመዝሙሮችና ግጥሞች ዝግጅት | ከየካቲት 5/99 - መጋቢት 10/99 |
| • መዝሙሮችንና ግጥሞችን ለሕብረተሰቡ ማሰማት መጀመር | ከመጋቢት 11/99 - ግንቦት 30/99 |
| • ድራማዎችን በአየር ላይ ማዋል | ከሚያዚያ 20 - ግንቦት 30/99 |
| • በቴሌቪዥን ተከታታይ መግለጫዎችንና ውይይቶችን ማድረግ | ከመጋቢት 20፣ ሚያዚያ 20፣ ግንቦት 1 እና ግንቦት 19/99 |
| • በተለያዩ ጋዜጦች ላይ የቆጠራ መልዕክቶችና ማስታወቂያዎች እንዲታተሙ ማድረግ | ከሚያዚያ 1- ግንቦት 30/99 |
| • ግንቦት 17 ቀን በአገሪቱ ከፍተኛ በባለስልጣናት ወይም በማስኤ ዳይሬክተር ግንቦት 20 ቀን 1999 ዓ.ም. በአገሪቱ ፕሬዚዳንት መግለጫ እንዲሰጥ ማድረግ | ግንቦት 17/99<br>ግንቦት 20/99 |
| • ለተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች ስለቆጠራው ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት | ከመጋቢት 15-25/99 |
| • መሪ መልዕክት በቴሌቪዥን በየቀኑ እንዲተላለፍ ማድረግ፡- | ከሚያዚያ 1- ግንቦት 30/99 |
| • ቡሮሹሮችን በተመለከተ ኮሚሽን አባላት እንዲዳረስ ማድረግ በኋላ ለፌዲራል ቢሮዎች ደግሞ በቁጥር 4 እንዲሰጥና ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ቡሮሹሮች በሚታይ ስፍራ ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲለጠፉ ማድረግ፣ | |

### 4.1.2 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቅስቀሳ የሚዲያ ኮሚቴ

ይህ ኮሚቴ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት፣ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ ከሬድዮ ፋና፣ ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተውጣጡ ሰባት አባላት ይኖሩታል:: ሃላፊነቱም:-

- በአገር አቀፍ ደረጃ በመገናኛ ብዙሃን የሚካሄደውን የትምህርትና ቅስቀሳ ተግባር በተቀናጀ መንገድ እንዲካሄድ ያስተባብራል፣ ፕሮግራም ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል::
- የሕዝብና ቤት ቆጠራው የዝግጅት ስራዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ እንዲታወቁ ያደርጋል::
- የቆጠራው ሂደት የሚዲያ ሽፋን በአግባቡና በወቅቱ እንዲያገኝ ያደርጋል::

የሚዲያ ኮሚቴ የሚያከናውናቸው ዝርዝር ተግባራት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

| ተ.ቁ | ሊካሄዱ የታቀዱ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች | የክንው ጊዜ ሥራው የሚጀመርበት ጊዜ | ሥራው የሚጠናቀቅበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ለመንግሥት የግል መገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች ስለቆጠራው ትምህርትና ቅስቀሳ የግማሽ ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ኘሮግራም | 18/7/1999 | 18/7/1999 |
| 2 | የቆጠራውን መሪ መልዕክት ሬዲዮ፣በቴሌቪዥንና በጋዜጣ በሳምንት ቢያንስ 3 ቀን በተለያዩ ቋንቋዎች | 1/8/1999 | 30/9/1999 |
| 3 | በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የተዘጋጁ ግጥሞችና በሬዲዮ፣በቴሌቪዥንና በጋዜጣ ማስተላለፍ፣ | 1/8/1999 | 30/9/1999 |
| 4 | በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የተዘጋጁ ድራማዎችን በአማርኛ፣ኦሮምኛና ትግሪኛ ቋንቋ የተዘጋጁትን በቴሌቭዥንና በሬዲዮ ማስተላለፍ | 21/8/1999 | 30/9/1999 |
| 5 | በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ለቅስቀሳ የተዘጋጁ የጋዜጣ መልዕክቶችን (በመጀመሪያ ገጽና በውስጥ ገጽ ) እንዲታተሙ ማድረግ፣<br>⇒ ፊት ገጽ ላይ በሳምንት 3 ጊዜ በጠቅላላው እስከ 21 ቀን<br>⇒ ውስጥ ገጽ ላይ በሳምንት 1 ቀን በጠቅላላው እስከ 10 ጊዜ | 20/7/1999 | 30/9/1999 |
| 6 | በጋዜጣ ልዩ እትም/ዘገባ/ ማውጣት (በሁሉም ቋንቋ) | 18/9/1999 | 18/9/1999 |
| 7 | በቆጠራው ዋና ዋና የዝግጅት ቀናት ልዩ ዘገባዎችን በስፋት ማቅረብ፡-<br>⇒ የመጀመሪያ ዙር ሥልጠና (አዲስ አበባ)<br>⇒ 2ኛ ዙር የአሰልጣኞች ሥልጠና (በየክልሉ ሥልጠና ጣቢያዎች)<br>⇒ 3ኛ ዙር የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ሥልጠና (በየክልሉ ሥልጠና ጣቢያዎች) | 03/8/1999<br>18/8/1999<br>03/9/1999 | 11/8/1999<br>30/8/1999<br>15/9/1999 |
| 8 | የመጨረሻዎቹ ዝግጅቶችን ሰፊ ሽፋን በመስጠት ማቅረብ፡-<br>⇒ የቤቶችና የቤተሰቦች ምዝገባ<br>⇒ የቆጠራ ዋዜማ ምሽት<br>⇒ ከቤት ቤት በመሄድ መረጃ መሰብሰብ | 18/9/1999<br>20/9/1999<br>21/9/1999 | 19/9/1999<br>20/9/1999<br>29/9/1999 |
| 9 | የፓናል ውይይት<br>አንደኛው በቆጠራው አፈጻጸም ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ<br>ሁለተኛው በቆጠራው ጥቅም ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማስፋት፣ | 25/8/1999<br>10/9/1999 | 30/8/1999<br>17/9/1999 |
| 10 | በከፍተኛ አመራር አካላት ጋዜጣዊ መግለጫ ማዘጋጀት | 17/9/1999 | 17/9/1999 |
| 11 | የሕዝብ አስተያየት ማሰባሰብ/Public Opinion/ ከተቻለ በሁሉም የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን | ግንቦት መጀመሪያ | ቆጠራው እስኪጠናቀቅ ድረስ |
| 12 | የኘሬዚዳንት ወይም ሌላ ከፍተኛ የመንግሥተ ባለሥልጣን ንግግር | ግንቦት 20/1999 ዓ.ም. ምሽት ላይ | |
| 13 | በቆጠራው የመጀመሪያ ቀን ለአርአያነት ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የሃይማኖት መሪዎች ሲቆጠሩ በቀጥታ ለህብረተሰቡ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ማስተላለፍ፣ | ግንቦት 21/1999 ዓ.ም. ጠዋት | |
| 14 | ስለሕዝብና ቤት ቆጠራ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ዶክመንተሪ አዘጋጅቶ ማቅረብ | 15/8/1999 | 30/8/1999 |
| 15 | በተመረጡ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ኘሮግራሞች ላይ ቆጠራውን አስመልክቶ ትምህርታዊና አዝናኝ መልዕክት ማስተላለፍ<br>ለምሳሌ፡- ታሜልሶን ኮሙኒኬሽን<br>የተማሪዎች ጥያቄና መልስ | 1/8/1999 | 30/8/1999 |
| 16 | በኘላዝማ በመጠቀም ስለቆጠራው ለተማሪዎችና አስተማሪዎች ግንዛቤ ማስጨበጥ | 25/7/1999 | 25/8/1999 |
| 17 | ዜና መጽሔትና ቴሌ ኮንፍረንስ ማካሄድ | 7/9/1999 | 22/9/1999 |

## 4.2 በክልል ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የክልሉን ነዋሪ ሕዝብ ስለ ቆጠራው ምንነት ዓላማና ጥቅም በማስረዳት በቂ ግንዛቤ አግኝቶ ተባባሪ እንዲሆን ለማድረግ በተላለፈው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ መሠረት በክልሉ ለሚገኙ ዞኖች መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ መ/ቤቶች ድርጅቶችና በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ በሚግባባበት ዋነኛ ቋንቋ የተለያዩ የቅስቀሳ መድረኮችንና አመቺ የሆኑ የቅስቀሳ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ቅስቀሳ ማድረግ፤

ለ. በዞን እንዲሁም በተዋረድ በወረዳና በቀበሌ ሕዝቡ ስለቆጠራው ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ትብብርና ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል የቅስቀሳውን ሥራ ተግባራዊ የሚያደርጉ የቅስቀሳ ኮሚቴዎች መደራጀታቸውን፣ መዋቀራቸውን እንዲሁም የቅስቀሳው ሥራ በተገቢው ሁኔታ መከናወኑን መከታተል፤

ሐ. ከሀገር አቀፉ ኮሚሽን ጽ/ቤት ተዘጋጅተው ለክልሉ የሚላኩ የቅስቀሳ ፖስተሮች፣ ብሮሹሮች፣ መፈክሮች፣ ድራማና መዝሙሮች በተዋረድ ለዞንና ለወረዳ በተገቢው ጊዜና ወቅት መሰራጨታቸውንና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን መከታተል፤

መ. የክልሉን የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሥራ አፈፃፀም ሂደትና እንቅስቃሴ፤ ስብሰባዎችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም መመሪያዎችን ለዞንና ለወረዳው ሕዝብ በተለያዩ መረጃ ማስተላለፊያና የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ማሳወቅ፤

ሠ. የቆጠራ ቀን በዓል በዞንና በወረዳ እንዲከበር ማድረግና በዓሉን ምክንያት በማድረግ በዕለቱ የሕብረተሰቡን ትብብርና ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችሉ የቆጠራው ማብሰሪያ ፕሮግራሞችንና ዝግጅቶችን በማድረግ ማሳወቅና መቀስቀስ፤

ረ. ሕብረተሰቡ ስለቆጠራው ዓላማና ጥቅም ተረድቶ በዞንና በወረዳ ለተመደቡ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ትክክለኛና ተገቢውን መረጃ በመስጠት ረገድ ትብብርና ድጋፍ እንዲያደርግ መቀስቀስ፤

### 4.2.1 የክልሉ ኮሚሽን በተለይ ለቅስቀሳው የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መርሃ ግብር ከዚህ በታች የተገለፀው ይሆናል:-

- ፖስተሮችና ብሮሹሮች ማሰራጨት:- ከሚያዚያ 15 - ግንቦት 21/1999 ዓ.ም.
- የክልል ሬዲዮ ጣቢያዎችን በመጠቀም ግጥሞችን፣ ድራማዎችንና መዝሙሮችን በተለያዩ ቀናት ማሰማት:- (ለምሳሌ ሚያዚያ 15፣ ሚያዚያ 30፣ ግንቦት 5፣ ግንቦት 19፣ ግንቦት 20፣ ግንቦት 25/1999 ዓ.ም.)
- መዝሙሮችና ግጥሞች በተለያዩ አመቺ መንገዶች ለሕብረተሰቡ እንዲሰሙ ማድረግ ሚያዚያ 1/1999 - ግንቦት 30/1999 ዓ.ም.
- የክልሉ የቆጠራ ሥራ ሂደትን አስመልክቶ በቴሌቪዥን ተከታታይ መግለጫዎችን መስጠት:- ሚያዚያ 25፣ ግንቦት 5፣ ግንቦት 15/1999 ዓ.ም.

- ግንቦት 20 ቀን 1999 ዓ.ም. የየክልሉ ፕሬዚዳንቶች ቆጠራውን አስመልክቶ በሬዲዮና በቴሌቪዥን መግለጫ እንዲሰጡ ወይም መልዕክት እንዲያስተላልፉ ማድረግ፣
- ብሮሹሮችን በተመለከተ ለዞን ኮሚሽን አባላት ይታደላል፣ በኋላ ለዞን ቢሮዎች ደግሞ በቁጥር 4 እንዲሰጥና ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ብሮሹሮች በሚታይ ስፍራ ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲለጠፉ ማስደረግ፣

## 4.3 በዞን ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የዞኑን ነዋሪ ሕዝብ ስለ ቆጠራው ምንነት፣ ዓላማና ጥቅም በማስረዳት በቂ ግንዛቤ አግኝቶ ተባባሪ እንዲሆን ለማድረግ በተሰጠው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ መሠረት በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ ወረዳና ቀበሌዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች እንዲሁም ሕብረተሰቡ በሚግባባበት ዋነኛ ቋንቋ የተለያዩ የቅስቀሳ መድረኮችንና አመቺ የሆኑ የቅስቀሳ ዘዴዎችን በመጠቀም ቅስቀሳ ማድረግ፣

ለ. በወረዳው በተዋረድም በቀበሌ ሕዝቡ ስለቆጠራው ያለው ግንዛቤ እንዲጨምርና ለቆጠራው ተገቢውን ትብብርና ድጋፍ እንዲሰጥ የቅስቀሳውን ሥራ ተግባራዊ የሚያደርጉ የቅስቀሳ ኮሚቴዎች መደራጀታቸውንና የቅስቀሳው ተግባር እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ. በክልሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት አማካኝነት ለዞንና ለወረዳ የተላኩ የቅስቀሳ ፖስተሮች፣ ብሮሹሮች፣ መፈክሮችና ሌሎች ለቅስቀሳ የሚረዱ ማቴሪያሎች ለተገቢው አገልግሎት በጊዜውና በወቅቱ መሰራጨታቸውን መከታተል፣

መ. ተንጠልጣይ መፈክሮች፣ ባነሮችና ስቲከሮች ተዘጋጅተው ለየወረዳውና ለከተሞች እንዲሰራጩ ማድረግ፣

ሠ. የዞኑን ኮሚሽን ጽ/ቤት የሥራ ሂደት እንቅስቃሴ፣ ስብሰባዎችና የተላለፉ ውሳኔዎች፣ የሥራ አፈፃፀም መመሪያዎች ከህብረተሰቡ ስለሚጠበቀው ትብብርና ተሳትፎ ለወረዳና ለቀበሌ ቅስቀሳ ኮሚቴዎች በተለያየ የመረጃ ማስተላለፊያና የቅስቀሳ ዘዴዎች በመጠቀም በመርሃ ግብሩ መሠረት መፈጸሙን መከታተል፣

ረ. የቆጠራ ቀን በዓል በወረዳና በቀበሌ እንዲከበር ማድረግና በዓሉን ምክንያት በማድረግ፣ የህብረተሰቡን ትብብርና ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችል ቅስቀሳ መከናወኑን መከታተል፣

4.3.1 በዞን ደረጃ የተቋቋመው የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ በቅስቀሳው ዘርፍ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መርሃ ግብር ከዚህ በታች የተገለፀው ይሆናል፡-

- ፖስተሮችንና ቡሮሹሮችን ማሰራጨት፡- ከሚያዚያ 15 - ግንቦት 20/1999 ዓ.ም.
- ተንጠልጣይ መፈክሮችና ባነሮችን አዘጋጅቶ ማሰራጨት፡- ከሚያዚያ 20 - ግንቦት 18/1999 ዓ.ም.
- መዝሙሮችና ግጥሞችን በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪዎች፣ በአውቶቡስ ተራዎች፣ በት/ቤቶች እና በዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ በተለያዩ ቀናት እንዲደመጡ ማድረግ፡- (ለምሳሌ ግንቦት 5፣ 10፣ 15፣ 20-28/1999 ዓ.ም.)
- ቡሮሹሮችን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የዞን ኮሚሽን አባላት ማደል፣ ለወረዳ ቢሮዎች ደግሞ በቁጥር 4 ቡሮሹሮችን እንዲሰጥና ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ቡሮሹሮች በሚታይ ስፍራ ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲለጠፉ ማድረግ፣ እንዲሁም በሁሉም ት/ቤቶች በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ እንዲለጠፉ ማስደረግ

## 4.4 በወረዳ ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ስለቆጠራው ምንነት፣ ዓላማና ጥቅም የወረዳው ነዋሪ በማስረዳት በቂ ግንዛቤ አግኝቶ ተባባሪ እንዲሆን ለማድረግና በተሰጠው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ መሠረት በወረዳው ውስጥ ለሚገኙ ቀበሌዎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶች ድርጅቶችና ሕብረተሰቡ በሚገባው ዋነኛ ቋንቋ የተለያዩ የቅስቀሳ መድረኮችንና ዘዴዎችን በመጠቀም ቅስቀሳ ማድረግ፣

ለ. በቀበሌ በተዋረድም ከሕብረተሰብ እስከ ግለሰብ ድረስ ስለ ቆጠራው በቂ ማብራሪያና ገለፃ በማድረግ ለቆጠራው ያለውን ተሳትፎ ጨምሮ ትብብርና ድጋፍ እንዲሰጥ ለማስቻል የቅስቀሳ ሥራውን ተግባራዊ የሚያደርጉ የከተማና የገጠር ቀበሌ የሕዝብ ቅስቀሳ ኮሚቴዎች ተደራጅተው የቅስቀሳውን ተግባር ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ. ከዞን የቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ለወረዳና ለቀበሌ የሚላኩ የቅስቀሳ ፖስተሮች፣ ቡሮሹሮች፣ መፈክሮችና ሌሎች ለቅስቀሳው የሚረዱና የተዘጋጁ ማቴሪያሎች በተገቢው ጊዜና ወቅት ለቅስቀሳው ተግባር መዋላቸውንና መሰራጨታቸውን፣ መከታተልና ማረጋገጥ፣

መ. የወረዳው የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሥራ ሂደትና እንቅስቃሴ፤ የተላለፉ ውሳኔዎችና የሥራ አፈፃፀም መመሪያዎች፤ ከቀበሌዎችና ከህብረተሰቡ ስለሚጠበቀው ትብብርና ተሳትፎ ለቀበሌ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቅስቀሳ ኮሚቴዎች መገለጻቸውንና መተላለፋቸውን መከታተል፤

ሠ. የቆጠራ ቀን በዓል በወረዳው ዋና ዋና ከተሞችና በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች እንዲከበር ማድረግና በዓሉን ምክንያት በማድረግ በቆጠራው ተሳታፊ የሚሆኑ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች የሕዝቡን ትብብርና ድጋፍ ለማግኘት እንዲችሉ ገለፃና ማብራሪያ የሚሰጥበት ዝግጅት እንዲኖር የቅስቀሳ መድረክ መፍጠር፤

4.4.1 በወረዳ ኮሚሽን ጽ/ቤት የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ለቅስቀሳው የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መርሃ ግብር ከዚህ በታች የተገለፀው ይሆናል፡-

- ፖስተሮችና ቡሮሹሮች ማሰራጨት፡- ከሚያዚያ 30 - 20/1999 ዓ.ም.
- ተንጠልጣይ መፈክሮችንና ባነሮችን ማሰራጨት፡- ከግንቦት 10 - 15/1999 ዓ.ም.
- መዝሙሮችንና ግጥሞችን በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪዎች፣ በአውቶቡስ ተራዎች፣ በት/ቤቶችና አመቺ ስፍራዎች በተለያዩ ቀናት እንዲደመጡ ማድረግ፣ ግንቦት 5፣ 10፣ 15፣ 18፣ 19፣ 20-29/1999 ዓ.ም.
- የቆጠራው ቀን በከተማ ደረጃና በገጠር ቀበሌ ደረጃ እንዲከበር ማድረግ፣
- ቡሮሹሮችን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የወረዳ ኮሚሽን አባላት ማደል፣ ለወረዳው ቢሮዎች ደግሞ በቁጥር 4 እንዲሰጥና ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ቡሮሹሮች በሚታይ ስፍራ ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲለጠፉ ማድረግ፣ እንዲሁም በወረዳው በሚገኙ ት/ቤቶች ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ እንዲለጠፉና በወረዳው በሚገኙ የገበያ ቦታዎች፣ የአውቶብስ መናኸሪያዎች እና ዋና ዋና መንገዶች እንዲበተኑ ማድረግ፣

## 4.5 በቀበሌ ደረጃ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የቀበሌው ነዋሪ ስለቆጠራው ምንነት፣ ዓላማና ጥቅም ተረድቶ እንዲተባበር፣ በተላለፈው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ መሠረት በቀበሌ ውስጥ ለሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ መ/ቤቶች ድርጅቶችና ሕብረተሰቡ በሚገኝባቸው አመቺ መድረኮች የቅስቀሳ ዘዴዎች መቀስቀስ፣

ለ. የቀበሌው ነዋሪ በቆጣሪነትና በተቆጣጣሪነት ለተመደቡ የቆጠራው ሠራተኞች በሩን ክፍት አድርጐ በመጠበቅ ትክክለኛና ተገቢውን መረጃ በመስጠት ራሱንና ቤተሰቡን እንዲያስቆጥር መቀስቀስ፣

ሐ. የቆጠራው ማብሰሪያ ቀን በዓል በቆጠራው ዋዜማ ዕለት ስለሚከበር በዕለቱና በተከታይ 10 ቀናት ውስጥ በሚደረገው ቆጠራ ሕዝቡ ራሱንና ቤተሰቡን ማስቆጠር እንዳለበት፣ የሚሰበሰቡት መረጃዎችም በምስጢር/ሚስጥር የሚያዙ ስለመሆናቸው፣ እያንዳንዱ ሰው መቆጠር ያለበት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑንና በድጋሚ መቆጠር ችግር እንደሚያስከትል ኗሪው እንዲያውቀው ማድረግ፣

መ. ከላይ የተጠቀሱት ጥረቶች ሁሉ ተደርገው ለቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ራሱንና ቤተሰቡን ለማስቆጠር የማይተባበር ቤተሰብም ሆነ ግለሰብ ካጋጠመ በአዋጅ በተሰጠው ድንጋጌ መሰረት የቅጣት እርምጃ እንደሚወሰድበት ማሳወቅና፣ ማስጠንቀቅ፤ ይህ ሁሉ ጥረት ተደርጐ ተባባሪ ካልሆነ ለሕግ ማቅረብና እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ማድረግ፣

4.5.1 በቅስቀሳ ወቅት በቀበሌ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መርሃ ግብር ከዚህ በታች የተገለፀው ይሆናል:-

- በቆጠራው ዕለትና በተከታይ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ህብረተሰቡ ራሱንና ቤተሰቡን እንዲያስቆጥር በድምጽ ማጉያ ማሳወቅና በተለያዩ ቀናት ማስደመጥ:- ግንቦት 10፣ 15፣ 18፣ 19፣ 20/1999 ዓ.ም.
- ፖስተሮች በቀበሌው ዋና ዋና ስፍራዎችና ጎዳናዎች መለጠፋቸውን ማረጋገጥ:- ግንቦት 15 - 20/1999 ዓ.ም.
- ቡሮሹሮችን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የቀበሌ ኮሚቴ አባላት ከታደለ በኋላ ለቀበሌ ጽ/ቤቶች ደግሞ በቁጥር 4 ቡሮሹሮች እንዲሰጥና ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ቡሮሹሮች በሚታይ ስፍራ ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲለጠፉ ማድረግ፣ እንዲሁም በቀበሌው በሚገኙ ት/ቤቶች ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ እንዲለጠፉና በቀበሌው በሚገኙ የገበያ ቦታዎች፣ የአውቶብስ መናኸሪያዎችና ዋና ዋና መንገዶች እንዲበተኑ ማድረግ፣

## 5. ሁሉም ሊያውቃቸው ስለሚገቡ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርሆዎች

ሦስቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቋሚ መርሆዎች የሚከተሉት ሲሆኑ በሁሉም ደረጃዎች ተገቢው ማብራሪያና ገለፃ መደረጉን ሕብረተሰቡም እንዲረዳው ማድረግ ያስፈልጋል::

- ማንኛውም የቤተሰብ አባል መቆጠር አለበት፣
- አንድ ሰው ሊቆጠር የሚገባው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፣
- ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች በሚስጥር የሚጠበቁ ናቸው::

## 6. የቆጠራ ቀን በዓል አከባበርን በተመለከተ ሊደረጉ የሚችሉ ተግባራት፤

**በቀበሌ ደረጃ (ከተማ):-**

- እንደሁኔታው የ3-5 ቀበሌዎች ወይም የከተማውን ህዝብ በአዳራሾች/ በስቴዲዮም ለስብሰባ በመጥራት የከተማው፣ የወረዳው ባለስልጣናት ስለቆጠራው ዓላማ ንግግር እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- በከተማው የተመደቡ ቆጣሪዎች፣ ተቆጣጣሪዎች እና ሌሎች ሠራተኞች የወረዳው የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ አባላት፣ ሻማ በማብራት በከተማው እንዲዘዋወሩ ማድረግ፣
- በተጨማሪም በድምጽ ማጉያ የቆጠራ መዝሙር ማሰማት፣

**በቀበሌ ደረጃ (ገጠር):-**

- የቀበሌውን ነዋሪ ሕብረተሰብ ስብሰባ በመጥራት ስለቆጠራው ዓላማ፣ ጥቅም፣ ከህብረተሰቡ ስለሚጠበቀው ድጋፍና ትብብር ...ወዘተ በቆጠራ ኮሚቴ አማካኝነት መግለጫ መስጠት፣

## 7 የመዝሙር አጠቃቀም

ለ1999 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትምህርትና ቅስቀሳ እንዲውሉ በተወዳዳሪዎች ከቀረቡ አስራ አራት /14/ መዝሙሮች መካከል ሦስት /3/ ተመርጠዋል:: እነዚህም መዝሙሮች በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ሲሆን ርዕሳቸውም፣

1. የሕዝብና ቤት ቆጠራ
2. ቆጠራ ልማት ነው
3. የሕዝባችን ብዛት ይታወቅ ተለይቶ የሚሉ ናቸው::

በተራ ቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰው መዝሙር በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ቆጠራን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ዝግጅቶች ማጀቢያ ሆኖ እንዲያገለግል ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ለኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ለFM እና ለፋና ሬዲዮ ተሰጥቷል::

ከተራ ቁጥር 1-3 ከተገለጹት መዝሙሮች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ እንደ ሁኔታው ዞን እና ወረዳ በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት አማካይነት ወደሚመለከተው አካባቢ ደርሶ በተለያየ መንገድ ህብረተሰቡ እንዲያዳምጠው ይደረጋል:: መዝሙሮች እንዲደመጡ ከሚደረግባቸው ቦታዎች መካከል ስብሰባዎች፣ የትምህርት ቤቶች ሚኒ ሚዲያ፣ አውቶቡስ ተራዎች ጥቂቶቹ ሲሆኑ በተጨማሪም በቆጠራው ዋዜማና በቆጠራ ቀናቶች በመኪና በመዘዋወር እንዲደመጡ ማድረግ ይገባል::

## 8. የፖስተሮች አጠቃቀምና ስርጭት

የ1999 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ከሚከናወንባቸው መንገዶች አንዱ ቆጠራውን ስዕላዊ በሆነ መግለጫ ህብረተሰቡን ማስተማር ሲሆን፣ ለዚህም ሲባል 5 (አምስት) ፖስተሮች በተለያዩ አምስት (5) ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣በአፋርኛና በሶማሊኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተዋል::

እነዚህም ፖስተሮች በየቀበሌው ስድስት፣ ስድስት ከየፖስተሩ ዓይነት እንዲዳረሱ የታሰበ ሲሆን ሕዝብ በሚሰበሰብባቸውና ሊያያቸው በሚችልባቸው ቦታዎች መለጠፍ ይኖርባቸዋል::

ነገር ግን በተለይ የዞን የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን (ሕ.ቆ.ኮ) ጽ/ቤት ኃላፊዎች በወረዳ ካርቶኖች ውስጥ ከሚገኙ ፖስተሮች ውስጥ የስልጠና ማዕከሎች የሚገኙበትን ከተማ የፖስተር ድርሻ አስቀድሞ በማውጣት የተወሰነ ኮፒዎችን የቆጠራው ቀን ሳይጠብቁ መለጠፍ ይችላል::

## 9. የብሮሹር አጠቃቀምና ስርጭት

ለ1999 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ እንዲረዱ ከተዘጋጁ ማቴሪያሎች አንዱ ብሮሹር ነው። ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስለ ቆጠራው ዋና ቁም ነገሮች በጥያቄና መልስ መልክ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በትግርኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀው ብሮሹር ይታደላል።

ብሮሹሮቹ በብዙ ኮፒ ታትመው በቆጠራው ሥራ ማስፈፀም ላይ ለተሰማሩ አካላት እና ለህዝቡ እንደሚሰራጩ ይታሰባል። ብሮሹሩ በቅድሚያ እንዲደርሳቸው ከሚታሰቡ አካላት ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ የሕ.ቆ.ኮ አባላት፣ የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞን፣ እና የወረዳ ቢሮዎች፣ትምህርት ቤቶች እና ኗሪዎች ይገኙበታል። የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላት እና ሌሎች ኮሚቴዎች ለእያንዳንዳቸው አንድ ኮፒ፣ እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት ቢሮዎች፣ ኃላፊዎች አንድ አንድ ኮፒ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት ቢሮ ሠራተኞች፣ በየቦታው ለሚገኙ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች የሚለጠፍ፣ ሁለት ሁለት ኮፒ በየትምህርት ቤት ማስታወቂያ ቦርድ ላይ የሚለጠፍ፣ ሁለት ሁለት ኮፒ አማካይ በሆኑ ልዩ ልዩ ቦታዎች የሚለጠፍ፣ እንዲሁም በየቀበሌው 15 ኮፒ እንደሚደርስ ታስቦ ተዘጋጅቷል። በተለይም ለትምህርት ቤቶች እንዲሠራጭ የታሰበው የቅስቀሳ ማቴሪያል ትምህርት ቤቶች ሳይዘጉ እንዲዳረስ ለማድረግ አስፈላጊው ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

## 10. ተጨማሪ የቅስቀሳ ማዕከላት/ስልቶች

የቆጠራውን መሪ መፈክሮች የያዙ /የሚያስተጋቡ/ ስቲከሮች ለምሣሌ በብሔራዊ በዓላት /ሚይ ዴይ ሚያዝያ 23/99፣ በሆስፒታሎች፣ ፋርማሲዎች፣ ክሊኒኮች፣ ጤና ጣቢያና ጤና ኬላዎች፣ በሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ በልዩ ልዩ የስፖርት ማዕከሎች /ስታዲየሞች/ በገበያ ማዕከላት፣ በአደባባዮች፣ በየትምህርት ቤቶች፣ በከተማ አውቶብሶች፣ በታክሲዎች /ከታክሲ ባለንብረቶች ወይም ባለንብረቶች ማህበር ጋር በመተባበር/፣ በኤግዚቢሽን ማዕከሎች፣ በሚኒስቴር መ/ቤቶች መዝናኛዎች፣ በግልና በመንግሥት ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ በማስልጠኛ ማዕከሎች፣ በአውቶብስ መናኸሪያዎች፣ በባቡር ጣቢያዎች፣ በአየር መንገድ ማረፊያዎች ወ.ዘ.ተ. በሌሎችም ሕዝብ በሚገኝባቸው የእንቅስቃሴ ማዕከላት።

## 11. ማጠቃለያ

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በጣም ከፍተኛ የሆነ ብሔራዊ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ከመሆኑም በላይ በአፈፃፀሙ የሀገሪቱን ነዋሪዎች በሙሉ ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጡ ማሳመንና የተለያዩ የሕዝብና የመንግስት አካላትን በማንቀሳቀስ ለሥራው ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማደራጀትና ማስተባበርን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባር ነው። ስለሆነም ለዚሁ ተግባር የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ መንግስት እንደ መጀመሪያውና ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ሁሉ የሶስተኛውን ሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማስፈፀም በአዋጅ ቁጥር

449/1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የተቋቋመ ሲሆን ተጠሪነቱም ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 449/1997 አንቀጽ 5 መሠረት ቆጠራውን ለማስፈፀም ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የቆጠራውን ሥራ ቅድመ ዝግጅቶችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ አሁንም ቀሪ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ከነዚህ ተግባሮች አንዱና ዋናው የትምህርትና ቅስቀሳ ተግባር በመሆኑ ዋናው ቆጠራ ከመጀመሩ ትንሽ ቀደም ብሎ ስለ ቆጠራው ዓላማና ጥቅም በቆጠራው ስለሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነትና ግለሰቦች የሚሰጡት መረጃ በምስጢር የሚጠበቁ ስለመሆኑ በተዘጋጀው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድና ሥራውን ለማስፈፀም በወጣው መርሃ ግብር መሠረት መከናወን ያለባቸው ተግባራት ለሕዝቡ መገለጽ ይኖርባቸዋል፡፡

የቆጠራው ቀን በዓል በዋዜማው ግንቦት 20/1999 ዓ.ም. ከተከበረ በኋላ ቆጠራው ከሚጀመርበት ከግንቦት 21 ቀን ጀምሮ ለ10 ቀናት በተከታታይ በቆጠራው ወቅት እያንዳንዱ ግለሰብ ሳይቆጠር እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይቆጠር በማብራራትና በማሳወቅ እያንዳንዱ ዜጋ ለቆጣሪዎችና ለተቆጣጣሪዎች ሊያደርግ ስለሚገባው ትብብርና ድጋፍ ማሳወቅና መግለጽ ዋነኛ ተግባራት ናቸው፡፡ ለዚህም ከላይ ከተገለጹት ተግባርና ሃላፊነቶች በተጨማሪ በትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ ላይ ከገጽ

29-33 የተጠቀሱት የተለያዩ አካላት ተሳትፎ፣ ትብብርና ድጋፍ ለቆጠራው መሳካት ወሳኝነት አላቸው፡፡

በአጠቃላይ የቆጠራው ሥራ የተሳካ እንዲሆን ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ተገቢውን ሁሉ ማድረግ በዋናነት በየደረጃው ከተቋቋሙት የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴዎች የሚጠበቅ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በየደረጃው ካሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ጋር በመመካከር እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታዎች ሌሎች የትምህርትና ቅስቀሳ ዘዴዎችን በመጠቀም ኅብረተሰቡንና ድርጅቶችን ለቆጠራው ሥራ መሳካት ተገቢው ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ማስተማርና መቀስቀስ እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡